STAY SAFE MN

# የCOVID-19 ክትባቶች እንዴት ይሰራሉ

12/16/2020

የመጀመሪያዎቹ የCOVID-19 ክትባቶች COVID-19 ቫይረስ ከተገኘ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መጥተዋል። ክትባት እንዴት በዚህ ፍጥነት እንደሚፈጠር ብዙ ጥያቄዎች አሉ። ከፌዴራል መንግሥት እገዛ ጋር ሂደቱ በፍጥነት እና በተሻለ ብቃት መከናወን ችሏል። ደህንነትን ለመፈተሽ የተደረጉ እርምጃዎች እንዳልተዘለሉ ማወቅ ያስፈልጋል። እነዚህ የጊዜ ሰሌዳዎች ሌሎች ክትባቶች ከሚሠሩበት ሂደት አንጻር የCOVID-19 ክትባቶች አሰራር እንዴት የበለጠ ውጤታማ እንደነበረ ያሳያሉ።

## ክትባቶች እንዴት ይሰራሉ

ክትባት የመስራት ሂደት እስከ 10 ዓመት ሊወስድ ይችላል።

- ምርምር ከተደረገ በኋላ፣ አንድ ክትባት በሦስት የሰው ሕክምና ጥናቶች ውስጥ ያልፋል፥ እያንዳንዱ ጥናት ከበፊቱ የበለጠ የሰው ብዛት ይኖረዋል።
- የሳይንስ አማካሪ ቡድናቸው የጥናቱን ውጤት ከገመገመ በኋላ የምግብ እና የመድኃኒት አስተዳደር (FDA) ክትባቱን ያፀድቃል።
- ከዚያ የብሔራዊ አማካሪ ቡድን፣ የበሽታ ምከታ እና ቁጥጥር ማዕከል (CDC) የክትባት ተግባራት አማካሪ ኮሚቴ (ACIP)፣ ክትባቱን ማን መውሰድ እንዳለበት ይመከራል።
- ከዚያ በኋላ፣ አምራቹ ክትባቱን መስራት ይጀምራል።
- ሰዎች ክትባቱን በሚወስዱበት ጊዜ፣ CDC እና FDA የክትባቱን የደህንነት መረጃን መመልከታቸውን ይቀጥላሉ።



# የCOVID-19 ክትባት እንዴት እየተሰራ እንዳለ

- ቀደም ሲል በኮሮናቫይረስ ላይ የተደረገው ምርምር እና በክትባት ቴክኖሎጂ ላይ የተደረጉ ግስጋሴዎች ይህን ሂደት በፍጥነት እንዲጀምር አድርጎታል።
- አንዳንድ ጊዜ ለክትባቱ ጥናቶች ገንዘብ መፈለግ ብዙ ጊዜ ሊወስድ ይችላል፣ ነገር ግን ለCOVID-19 ክትባት የፌዴራል መንግሥት ብዙ ገንዘብ አበርክቷል።
- አምራቾች እያንዳንዳቸው እስኪከናወኑ ከመጠበቅ ይልቅ፣ ለሦስቱም የሕክምና ክሊኒካዊ ጥናቶች ተሳታፊዎችን በአንድ ጊዜ መልምለዋል።
- ክሊኒካዊ ጥናቶቹ እየተካሄዱ አምራቾችም ደግሞ ክትባቱን እየሰሩ ይገኛሉ።
- ከድንገተኛ ጊዜ የመጠቀሚያ ፈቃድ (EUA) ጋር ክትባትን ማፅደቅ እንዲሁ አነስተኛ ጊዜ ይወስዳል። ደህንነቱ የተጠበቀ የሚሰራ ክትባት ማግኘት ቁጥር አንድ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው።
  - በፌዴራል ደረጃ ያሉ ቡድኖች ክትባቶችን ከመገምገም እና ምናልባትም ከማጽደቅ ምንም ነገር እንዲያዘገያቸው አልፈቀዱም። ለምሳሌ፣ FDA የግምገማ ሂደቱን ከወራት ወደ ሳምንታት ለማሳጠር ብዙ ሰራተኞችን ጨምሯል።
- ክትባቱ ማረጋገጫውን የሚያገኘው ጥናቶቹ ክትባቱ ደህንነቱ የተጠበቀ እና የሚሰራ መሆኑን ካሳዩ ብቻ ነው




አሁንም ቢሆን ስለ COVID-19 ክትባት መማር ያለብን ነገሮች አሉ፣ ለምሳሌ ክትባቱ ምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ እና በአጠቃላይ ህዝብ ውስጥ እንዴት እንደሚሰራ፣ ነገር ግን እነዚህ የCOVID-19 ክትባትን ለማዘግየት አስተማማኝ እና ውጤታማ ምክንያቶች አይደሉም።

ለበለጠ መረጃ፣ ኮቪድ-19 ክትባት (www.health.state.mn.us/diseases/coronavirus/vaccine.html) ይመልከቱ።

MINNESOTA

የሚኒሶታ ጤና መምሪያ | health.mn.gov | 651-201-5000
625 Robert Street North PO Box 64975, St. Paul, MN 55164-0975

ሌላ የፎርማት አማራጭ ለመጠየቅ health.communications@state.mn.us ያግኙ። (Amharic)